## የወሊጋ ፡ ለቀምት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ እንደተሰጠኝ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገረ ፡ ገዢዎ ችንና ፡ ዳኞችን ፡ ለየአገሩ ፡ እየመደቡ ፡ ሲሾሙ ፡ ለኔም ፡ ከፊታውራሪ ነት ፡ ማዕረግ ፡ ጋር ፡ የወሊጋ ፡ ለቀምት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ተሰጠኝ ፡፡ ለዚ ሁም ፡ የተጻፈልኝ ፡ የሹመት ፡ ማዘዣ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡፡



ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልዴ ፡ ዮሐንስ ፡
ፊታውራሪ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ቁጥር ፡ ፩፻፺፯ ፡
ሰኔ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ይድረስ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ለቀምት ፡ ወለጋን ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ መታዘዝዎንና ፡ የፊታውራሪነት ፡ ማዕረግ ፡ ለርስዎ ፡ መሰጠቱን ፡ በማክበር ፡ አስታውቅዎታለሁ ፡፡ አዲሱ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እስኪላክልዎ ፡ ድረስ ፡ ለርስዎ ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ ማስታወሻ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ይገኛል ፡፡

ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወ ፡ ዮሐንስ ፡
ማኅተም ፡
የጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡፡



እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ለለቀምት ፡ ሕዝብ ፡ የተጻፈው ፡ የግር ማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡፡

### የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፡፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡፡

### አ ዋ ጅ ፡፡

የለቀምት ፡ ሕዝብ ፡ ስማ ፤

በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በቸርነቱ ፡ ያደረገ ላትን ፡ ለማንም ፡ አገርና ፡ ሕዝብ ፡ አድርጎት ፡ አያውቅም ፡፡ ነጻነትዋን ፡ ከመመለስ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ የአንድነት ፡ ጥቅም ፡ እንድትመዝኑት ፡ አደረገ ፡፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የጠላታችንን ፡ ስብከትና ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ሲሰራ ፡ የነበረው ፡ ተንኰል ፡ አማራ ፡ ጎንደሬ ፡ ጎጃም ፡ እያለ ፡ ሁሉም ፡ የአንዲት ፡ እናት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ መሆናችሁን ፡ ለማስረሳትና ፡ በወገን ፡ ለያይቶ ፡ ለማስቀረት ፡ ነበር ፡፡ ምንም ፡ ብዙዎች ፡ ቢታለሉ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ጉዳቱን ፡ ለመመዘን ፡ ችለው ፡ ከጠላት ፡ ሲከ ላከሉ ፡ እስካሁን ፡ ቆዩ ፡፡ እኛም ፡ ደርሰንላቸው ፡ ጠላታችን ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ በዋና ፡ ከተማችን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ለመግባት ፡ በቃን ፡፡ ያለፈውን ፡ የአ ምስት ፡ ዓመት ፡ ሥራ ፡ ብትመለከቱ ፡ ቁጥራቸው ፡ ከጠላት ፡ እጅግ ፡ ያነሰ ፤ መሣሪያ ፡ ያልነበራቸው ፡ አርበኞቻችን ፡ አንድነት ፡ ስለነበራቸው ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፡፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ ልትገነዘቡት ፡ የምን ፈልገው ፡ የባዕድ ፡ ገዢ ፡ ያመጣውን ፡ ጉዳት ፡ ነው ፡፡ ባልተወለደ ፡ አን ጀቱ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ደጉን ፡ ሕዝባችንን ፡ ያለፍርድ ፡ አስደበደበው ፡፡ በመታደል ፡ ካመለጡት ፡ ከአንድ ፡ አንድ ፡ ባላባቶች ፡ በቀር ፡ ያገርን ፡ ወግና ፡ ሕግ ፡ ለማጥፋት ፡ ለሕዝባችንም ፡ ተቆርቋሪ ፡ ለማሳጣት ፡ ባላባ ቶችን ፡ ሁሉ ፡ እንደምታውቁት ፡ ፈጃቸው ፡፡ ለእጽማቸው ፡ ማረፊያ ፡ የተ ወለዱበትን ፡ አገር ፡ መሬት ፡ ተነፍገው ፡ በየሠፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ጣላቸው ፡፡ ለዚህም ፡ የዓይን ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ፡፡ ተረፉ ፡ የተባሉትንም ፡ ባላባ

አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባንዲራ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ሁለት ፡ የሃምሳ ፡ አለቆች ፡ ከግምባር ፡ አንድ ፡ የመቶ ፡ አለቃ፡ አደረግሁና ፤ ለመቶ፡ አለቃውም ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ ሲቃረቡ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ ባንዲራ ፡ እንዳታልፉ ፡ ያለፋችሁ ፡ እንደሆን ፡ መታኰሳችን ፡ ነው ፡ በልና ፡ ንገር ፡ ብዬ ፡ አዘዝኩ፡ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ ወደሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደቀረቡ ፡ የታዘዘውን ፡ ለኰሎኔልና ፡ ለፖለቲካል፡ ኦፊሰሩ ፡ ነገራቸው ፡ እነሱም፡ በማንገራበድ ፡ አስፈ. ራርቶ ፡ ያን ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ ነበርና ፡ ሃሳባቸው ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ የቆረጥን ፡ መሆናችንን ፡ ሲመለከቱ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ አፈገፈጉና ፡ በዙሪያችን ፡ ሠፈር ፡ አደረጉ ።


እኛም ፡ ያን ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ለለቀምት ፡ ባላባቶች ፡ እያካፈልን ፡ ሰጠንና ፡ ወደ ፡ ለቀምት ፡ ግዛት ፡ እንዲሻገርና ፡ ቦታ ፡ እንዲይዝ ፡ አደረግን ፤ እንግሊዞችም ፡ ከሶስት ፡ ቀን ፡ ክብ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሠፈራቸው ፡ ተመለሱ ። እኔም ፡ ከጉድጓድ ፡ ሳይወጣ ፡ የቆየውን ፡ እንዲጠበቅ ፡ አዘዝኩና ፡ ለየባላባቱ ፡ አከፋፍዬ ፡ የሰደድኩትን ፡ በደንብ ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ለቀምት ፡ ግዛት ፡ ተሻገርኩና ፡ ካሚዎን ፡ እንዲመጣ ፡ ጠይቄ ፡ የነበረውን ፡ ተጠባብቄ ፡ እንደመጣልኝ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላክሁና ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ዩብዶ ፡ ተመለስኩ ፡ እዚያም ፡ ስደርስ ፡ ያን ፡ በወታደር ፡ አስጠብቄ ፡ የሄድኩትን ፡ በጉድጓድ ፡ የነበረ ፡ የማሪትሬዝያ ፡ ብር ፡ ለጠባቂው ፡ የጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ብሎ ፡ የው ሸት ፡ ቴሌግራም ፡ አሳይቶ ፡ እምቢ ፡ ያልክ ፡ እንደሆን ፡ ንገረኝ ፡ መልሱን ፡ እንድልክ ፡ ብሎ ፡ አስፈራርቶ ፡ ሲነግረው ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጠብቅ ፡ የታዘዘው ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የጃንሆይ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ የውሸት ፡ ቴሌግራም ፡ አምኖ ፡ ተቀብሎ ፡ አስረክቦት ፡ ኖሮ ፡ በትእዛዝ ፡ አስረክብኩ ፡ ከጃንሆይ ፡ የመጣው ፡ ቴሌግራም ፡ ይኸውና ፡ ብሎ ፡ አቀረበልኝ ። ሐሰቱን ፡ ብረዳም ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ያን ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ ከነብር ፡ አፍ ፡ ፍየልን ፡ ለማስለቀቅ ፡ እንደማይቻል ፡ እንደዚሁም ፡ እንአጅሬ ፡ እጅ ፡ የገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሳልችል ፡ ቀረሁ ።

የሰጠኝም ፡ ምክንያት ፡ እኔ ፡ ወስጄ ፡ ለጃንሆይ ፡ አስረክባለሁ ፡ ማለትን ፡ ስለሆን ፡ አታሎ ፡ የወሰደ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ከመጻፍ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ሳላተርፍ ፡ ቀረሁ ፤ እንግዲህ ፡ እንግሊዞች ፡ በማታለል ፡ 90,000 ዘጠና ፡ ሺህ ፡ የማሪያ ፡ ትሬዛ ፡ ብር ፡ ሲወስዱ ፡ ተከላክለን ፡ ያስቀረነው ፡ ከጦር ፡ ሜዳ ፡ የተገኘ ፡ 350,000 (ሶስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ፡ ሺህ ፡ የማሪያ ፡ ትሬዛ ፡ ብርና ፡ 1,005 (አንድ ፡ ሺህ ፡ አምስት) ፡ ወቄት ፡ ወርቅና ፡ 800 ወቄት ፡ ብሪያንቲል ፡ (ነጭ ፡ ወርቅ) ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ተልኰ ፡ ሲገባ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ የማሪያ ፡ ትሬዛ ፡



ብር ፡ ለተቋረጡ ፡ መንገዶችና ፡ ለተሰበሩ ፡ ድልድዮች ፡ ማሠሪያ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ በለቀምት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ቀርቶ ፡ ስለነበረ ፡ የወለጋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ለኰሎኔል ፡ ዓቢይ ፡ አበበ ፡ ስለተሰጠ ፡ ይህን ፡ የቀረውን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ኰሎኔል ፡ ዓቢይ ፡ አበበ ፡ እንዲረከቡ ፡ ተደረገ ።

በእኔ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የጦር ፡ ጓደኞቻችን ፡ ማንገራበድና ፡ ማስፈራራት ፡ ከገለጽኩ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አገር ፡ ጠባቂ ፡ ባደረጓቸው ፡ ሹማምንቶች ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ማንገራበድና ፡ ማታለል ፡ እቀጥላለሁ ። እኔ ፡ ወደ ፡ ደምቢዶሎ ፡ የጠላትን ፡ ጦር፡ ለማጥቃት ፡ ስሄድ ፡ ለቀምትን ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ቀኛዝማች ፡ ዘውዴ ፡ መላትን ፡ (ዛሬ ፡ ደጃዝማች ፡ ) ትቼው ፡ ሄጄ ፡ ነበር ፤ እንደዚሁ ፡ እንግሊዞችም፡ አንድ፡ ካፕቴን፡ ዊልሞት ፡ የተባለ ፡ የፖለቲካ፡ ኦፊሰር ፡ ለቀምት ፡



ኰሎኔል ፡ ዓቢይ ፡ አበበ ፡

ከተማ ፡ አስቀምጠው ፡ ነበር ፡ ይህ ፡ የፖለቲካ ፡ ኦፊሰር ፡ እኔም ፡ የሾምኩትን ፡ እንደራሴ ፡ የአገሩንም ፡ ባላባቶች ፡ ወደ ፡ ጎን ፡ ተውና ፡ ጠላት ፡ ሾሟቸው ፡ የነበሩትን ፡ ሹማምንቶች ፡ ይዞ ፡ እየሰበከ ፡ እኔ ፡ የሾምኩት ፡ እንደራሴ ፡ ትእዛዙ ፡ እንዳይሰማ ፡ እያደረገ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ።

ይህ ፡ አልበቃ ፡ አለውና ፡ ከዕለታቱ ፡ በአንደኛው ፡ ቀን ፡ በቀኛዝማች ፡ ዘውዴ ፡ ወታደሮች ፡ ይጠበቅ ፡ የነበረውን ፡ መጋዘን ፡ ለብቻው ፡



ፊታውራሪ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ከወታደሮችና ፡ ከአርበኞች ፡ ጋር ። ወለጋ ፡ ከመጨረሻው ፡ ድል ፡ በኋላ ። በመካከል ፡ ፊታው-
ራሪ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በግራ ፡ ቀኛዝማች ፡ ዘውዴ ፡ ሙላት ። በቀኝ ፡ ቀኛዝማች ፡ ዘሪሁን ፡ ከበደና ፡ ሻለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ።





ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡

